# "ቢሞቱም - አልሞቱም!...."

*"ቢሞቱም አልሞቱም!.... እነሱስ ሠርተው ነው"*

*የምትንስ እኛ ነን፣ ስንሞት፣ ስንሞት፣ ስንሞት የኖረነው፤*

*ፍርሀት ነግሶብን፤ ቀኑን አጨልመን የቁም ሞት - የምትነው*

*ዓይነ-ስውርን እንኳ'፣ "ውጭ ጨለማ ነው! አትወጣም" እያልን፣ የምናስፈራረው።*

"ቢሞቱም አልሞቱም!...ቢሞቱም ሠርተዋል".......

ሀገርን የሚያከል፣ ሲያፈርሱ ኑረዋል!

ስብዕና ክብራችን፣ በዓለም አዋርደዋል!

ቅዱስ እምነታችን፣ ከድተው - አስክደዋል!

ህዝብንም ከፋፍለው፣ ድንበር አፍርሰዋል!

የንጹሀንን ደም፣ እንደ ውሀ አፍስሰዋል!

ኢትዮጵያዊነትን ያለ ዕረፍት ወግተዋል!

*"ቢሞቱም አልሞቱም!.... እነሱስ ሠርተው ነው"*

*የምትንስ እኛ ነን፣ ስንሞት፣ ስንሞት፣ ስንሞት የኖርነው፤*

*ፍርሀት ነግሶብን፤ ቀኑን አጨልመን የቁም ሞት - የምትነው*

*ዓይነ -ስውርን እንኳ'፣ "ውጭ ጨለማ ነው! አትወጣም" እያልን፣ የምናስፈራረው።*

የክህደት የተንኮል፣ የጥፋት ዘር - ዘርተው

ወጣት አዛውንቱን፣ ባዕድ ዓምላኪ አድርገው

ለህጻን ሳይራሩ፣ ለሰዶማዊያን ጉዲፈቻ ሸጠው

ዘርፈው - አዘርፈው፣ ሀገር-ታሪክ ገለው

እነሱስ ሄደዋል...... ስራቸውን ሰርተው

"መከሩን" ለትውልድ፣ ላ'ገር ልጆች ጥለው።

*''ቢሞቱም አልሞቱም!.... እነሱስ ሥርተው ነው’’*

*የምትንስ እኛ ነን፣ ስንሞት፣ ስንሞት፣ ስንሞት የኖረነው፤*

*ፍርሀት ነግሶብን፤ ቀኑን አጨልመን የቁም ሞት - የምትነው*

*ዓይነ-ስውርን እንኳ’፣ ” ውጭ ጨለማ ነው! አትወጣም” እያልን፣ የምናስፈራረው።*

''መከር'' መሰብሰቡን ግን ካወቅንበት

ከእንቅልፍ ከነቃን፣ ከህልም ዓለም ቅዥት

በልባችን ውስጥ፣ ካሳደርን ቅንነት

በራዕይ ተመርተን፣ ከተከተልን እውነት

እምባም ይጠረጋል፣ ሲፈስ ከኖረበት

ትውልድ ቀና ይላል፣ አንገት ከደፋበት

ድንበር ይመለሳል፣ ወደነበረበት

ለወገን ይሆናል፣ “የደማችን መሬት”

ሀገር ትነሳለች ከወደቀችበት።

ለጋራ ክብራችን ፣ በጋራ ኀላፊነት

ከቆምን በአ'ድነት፣ ለመሰዋዕትነት

የትውልድ መከራ፣ ''በቃ!'' እሚባልበት

ታሪክ እንሰራለን ፣ የማይሞት ብንሞት።

*''ቢሞቱም አልሞቱም!.... እነሱስ ሥርተው ነው’’*

*የምትንስ እኛ ነን፣ ስንሞት፣ ስንሞት፣ ስንሞት የኖረነው፤*

*ፍርሀት ነግሶብን፤ ቀኑን አጨልመን የቁም ሞት - የምትነው*

*ዓይነ-ስውርን እንኳ’፣ “ ውጭ ጨለማ ነው! አትወጣም” እያልን፣ የምናስፈራረው።*

ባደሙትም መጠን - አዎ!...ደም ይደማል

ባፈሰሱት መጠን - አዎ!... ደም ይፋሳል፤

ደምም - ደም ነውና፣ ደም - ደምን ይወልዳል::.....

ለእኩይ ምግባራቸው፣ ለሡሩብን ግፍ፣ መግለጫ አይገኝም

የዓለም ቋንቋ - ቃላት፣ አዕምሮ አይገለጸውም።

ግን ስንሰባስብ፣ ይቅር ስንባባል - ስንማማርብት

ያኔ ነው ሞታቸው፣ እውነተኛው ሞት - እሚቀበሩት፤

አብቦ ሲያፈራ "ከፋፍለን - ገድለነው፣ አጠፋነው" ያሉት

ህብረ - አንድነታችን............ ኢትዮጵያዊነት!።

---//----

ፊልጶስ / 13-08-2004

ኢሜል:philiposmw@gmail.com